# ለአክራሪ እስልምና ችግሮች - የእኛ መፍትሔዎች

*(ዲ/ን ኤፍሬም እሸቴ)*
ephremeshete@gmail.com

ይህ አነስተኛ የመወያያ ጽሑፍ በሚከተሉት ርእሶች ዙሪያ እንዲያጠነጥን ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። እነዚህ ዐበይት ርዕሶች የሚከተሉት ይሆናሉ።

*1. አክራሪ እስልምና ምንድር ነው?*

*2. የአክራሪነት ግብ፣*

*3. አክራሪዎች ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው የሚመለከቱት?*

*4. አክራሪ እስልምና የደቀነውን አደጋ ለመቋቋም ምን ማድረግ አለብን?*

ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹ዘመኑን ዋጁ›› ሲል ያስተማረን ትምህርት ዛሬ በዚህ በተቀደሰው ሥፍራ ተሰብስበን አገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን አደጋ ስለጋረጠው የዘመናችን ፈታኝ ችግር ለመነጋገር መሪ ቃላችን ሆኗል። ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት ከአይሁድ የገጠማትን ፈተና ለማለፍ ሰቃልያነ እግዚእ ያቀረቡትን ጥያቄ በአፍም፣ በመጣፍም ብላ ማቸነፍ ነበረባት። በዘመነ ሐዋርያውያነ አበውም እንዲሁ የግሪክን ፍልስፍና፣ የግኖስቲኮችን ኑፋቄ፣ የአርዮስንና የተረፈ አርዮሳውያንን ቅሰጣ እንዲሁ በትምህርቷ መቋቋም ነበረባት። በዘመነ ሰማዕታት ደግሞ አጥንቴን ለመንኮራኩር፣ አንገቴን ለሰይፍ በሚሉ ልጆቿ አማካይነት የክርስቶስን የምስራች ወንጌል በደሟ መስክራለች። በዘመናችን ደግሞ ተረፈ-ግራኞች ለቀሰቀሱት የቅሰጣና የሰይፍ እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያን መልስ እንድትሰጥ ትጠበቃለች።

+++

## 1ኛ) አክራሪ እስልምና ምንድር ነው?

አክራሪ እስልምና ወይም በአረብኛው ‹‹ኡሱል›› ተብሎ የሚታወቀው የእስልምና አስተምህሮ እስልምና ወደ ቀደመ ማንነቱና እምነቱ መመለስ አለበት፣ በቁርዓንና በሱና ላይ ብቻ መመርኮዝ አለበት የሚለው የእስልምና ክፍል የሚያራምደው ትምህርት ነው፡፡ በእስልምና ትምህርት መሠረት ቁርዓንና ሱናውን የመተርጎምና የማመስጠር ብቃት 10ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ቆሟል፣ ማንኛውም አስተማሪ ከዚያን ዘመን በፊት በተመሰጠረው ትርጉምና ፍቺ ላይ ተመርኩዞ ያስተምራል እንጂ አዲስ ትርጉም መስጠት አይችልም፡፡ ይህም መሠረታዊ ሐሳብ በአረብኛው *‹‹ታቅሊድ››* (يد) ይባላል፡፡[1] ቀጥተኛ ትርጉሙ ‹‹መከረጅ፣ መቅዳት፣ አስመስሎ መናገር፣ አንድን ሰው መከተል፣ to imitate›› ሊባል ይችላል፡፡ በጥንቱ ዘመን ያስተማሩ የእስልምና መምህራንን ትርጉም ያለምንም ጥያቄ መቀበልና መከተልን ይመለከታል፡፡ እምነታቸውን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምሁራኑ የተናገሩት የመጨረሻ መልስ ይሆናል፡፡ መጠራጠር ወይም ነገሩን አንብቦ ለመመርመር የሚደረግ ምንም ጥረት አይኖርም፡፡

የዚህ የ*‹‹ታቅሊድ››* ተቃራኒ የሆነው እስላማዊ አስተምህሮ ደግሞ ‹‹ኢጅቲሐድ››[2] የሚባለው ሲሆን የእስልምና መጻሕፍትን አንባቢው ባነበበውና በተረዳው መልክ መተርጎምን የሚፈቅድ ሐሳብ ነው፡፡ የእስልምና ሕግ መሠረቶች የሆኑትን ቁርዓኑንና ሱናውን የመተርጎሙን ሥልጣንና ኃላፊነቱን እንደ ጥንቱ ምሁራኑ ብቻ ያደርጉት ከነበረው ላይ አንስቶ ለተርታውም አማኝ ይሰጣል፡፡ ይህም በዘመናችን የሚታየውን የአክራሪነት መንፈስ ሊፈጥር በቅቷል፡፡ የዚህ የአክራሪነት ትምህርት ዋነኛ አራማጆች መካከል ግብጻዊው ሰይድ ኩትብ አንዱ ነው፡፡ ሰይድ ኩትብና ሌሎች አክራሪዎች እስልምናን በአዲስ መልክ መተርጎምን በመጀመር ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ አክራሪዎች ያዘጋጇቸው መጽሐፎቻቸው ዛሬ ወደ አማርኛ ተተርጉመው በይፋ በስፋት እየተሠራጩ ነው፡፡

ስለ አክራሪ እስልምና ለመነጋገር በጠቅላላው እስልምናንና በተለይም የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን በሁለት ክፍለን መመልከት ግድ ይለናል፡፡ የመጀመሪያው የእስልምና

---

[1] *‹‹ታቅሊድ››* በአረብኛው يد ይባላል፡፡

[2] አረብኛው اجتهاد ይለዋል፡፡

ክፍል ከኢትዮጵያ ክርስትና ጋር ተጎራብቶ፣ አያሌ የክርስትና ጠባዕያትን ተላብሶ በሰላም የኖረው ‹‹ሰላማዊው እስልምና›› ሲሆን ሌላው ደግሞ በግራኝ መንፈስ የሚሄደው፣ በሳዑዲት አረቢያ የገንዘብ ድጎማ የሚንቀሳቀሰው፣ በነ‹‹*ሰይድ ኩትብ*›› ፍልስፍና የሚመራው፣ በሰፕቴምበር 11 ቦንብ ፍንዳታ፣ በጅማና በምዕራብ ወለጋ ጭፍጨፋ ራሱን የገለጠው አክራሪ ቡድን ነው፡፡

ይህ ማለት ግን አክራሪ እስልምና ከእስልምና ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ባዕድ አስተሳሰብ አለመሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ እንደ ጎራዴና ሰገባ፣ እንደ ዳዊትና ማኅደሩ፣ አክራሪነት በእስልምና ውስጥ ተሸጉጦ ያለ የእስልምናው አንድ ክፍል ነው፡፡ አክራሪዎች ሙስሊሞች ናቸው እንጂ ሌላ እምነት አራማጆች አይደሉም፡፡[3] አክራሪዎቹን ከሌሎች ሙስሊሞች መለየቱ እንዲህ ቀላል ባይሆንም በደምሳሳው ግን ሳዑዲት አረቢያ የምታስፋፋው ‹‹ወሐቢዝም›› ወይም በሌላ አጠራሩ ‹‹ሳላፊያ›› (ተከታዮቹ ሳላፊዩን ይባላሉ) ዋነኛው ሉላዊ አክራሪነት (Global Terrorism and Fundamentalism) መሪ መሆኑን መጥቀስ ይገባል፡፡[4] የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ስለ ሁለተኛው የእስልምና ክፍል መነጋገር እንጂ ስለ ሰላማዊው የኢትዮጵያ እስልምናና ሙስሊም ማውሳት አይደለም፡፡

## 2ኛ) የአክራሪነት ግብ

የአክራሪዎች ግብ አንድና ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ ያነሰ ነገር አይቀበሉም፡፡ በእነርሱ አመለካከት የዚህች ዓለም ችግር ዓለም ከሸሪዓ ሕግ ተቃራኒ በሆነው ዓለማዊ ሕግ መተዳደሯ ነው፡፡ መፍትሔው ደግሞ ይህንን ‹‹ዓለማዊ ሕግ›› በመሻር በሸሪዓ መተካት ነው፡፡ በእነርሱ አመለካከት መጪው ዘመን ‹‹የእስልምና ብሩህ ዘመን ነው››፡፡ እንኳን ኢትዮጵያን ዓለምን (ያለንባትን አሜሪካን ጨምሮ) በሸሪዓ ሕግ ማስተዳደር ነው ዓላማቸውም ግባቸውም፡፡

---

[3] Fuller, Graham E., *The Future of Political Islam*, Palgrave MacMillan, (2003), p.48

[4] በኢትዮጵያ ‹‹ሳላፊያ›› የሚባል ጋዜጣ እንደሚታተም ያውቃሉ?

## 3ኛ) አክራሪዎች ኢትዮጵያን የሚመለከቱበት የፍልስፍናቸው መነጽር ምን ይመስላል?[5]

አክራሪዎች ለኢትዮጵያና ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን አመለካከት ለመረዳት ሁለት መጽሐፎቻቸውን በአማኝነት ጠቅሼ አብራራለሁ።

*ሀ. የመጀመሪያውና በዓሊ አል ሼይክ አሕመድ በክር የተጻፈው* ***«ወደ ኢትዮጵያ የተደረጉ የሁለቱ ሒጅራዎች መለያ ባሕርያት»*** የሚለው ባለ 258 ገጽ መጽሐፍ የሚከተሉትን ዐቢይ ሐሳቦች ያንጸባርቃል።

*1ኛ) ‹‹ነጃሺ›› እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት ኢትዮጵያ ሁል ጊዜም የእስላም አገር /ዳር አል-ኢስላም/ ልትኾን ችላለች።*

*2ኛ) ነጃሺ እስልምናን በመቀበሉ ምክንያት እስልምና በኢትዮጵያ ያገኘው ድል አልቀጠለም። ተሰናክሏል።*

*3ኛ) ‹‹ጨቋኙ ክርስትና እስልምናን በኢትዮጵያ አዋርዶታል ወይም በሌላ አነጋገር በጨቋኙ የክርስትና ሃይማኖት ምክንያት እስልምና በኢትዮጵያ ሊዋረድ ችሏል።››*

**የዚህንም ምክንያት እንደሚከተለው ያብራራዋል።**

> *‹‹ክርስቲያኖች ሁልጊዜም የኢስላም አል ነጃሺን ታሪክ ይክዳሉ። ለእስልምና ያላቸው ጥላቻ ወሰን የለውም። ነጃሺ ገና ለጋ በነበረበት ዘመን እስልምናን መረጠ። በርግጥ ከሰሐባዎች ጋር ከመገናኘቱ በፊት ጨቋኙን የክርስትና ትምህርት ይከተል ነበር። ሰሐባዎችን ሲያገኝ የክርስትናን ጨቋኝነት ተቃውሞ እስልምናን ተቀበለ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን በዚያው በጨቋኝ ትምህርቷ ቀጥላለች። ካህናቱ ነጃሺ ያደረገውን ምግባረ ሠናይ በመቃወም ተዋጉት። በቅርቡ ዘመንም ክርስቲያኖች ይህንኑ ታሪክ በልጅ ኢያሱ ላይ ደገሙ። ከምዕራባውያን ልዕለ ኃያላን ጋር በመመሳጠር ሙስሊሙን ንጉሥ ከሥልጣኑ አፈናቀሉት። በነጃሺ እና በልጅ ኢያሱ ታሪክ የምናየው ተመሳሳይ የኾነ የካህናቱን ኀያልነት ነው። ካህናቱ በጥላቻ የተሞሉ፣ ትዕግሥት የለሾች ናቸው። ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ካህናት ሁሉ፣ በየትም ቦታ ቢኖሩ የጋራ መገለጫቸው ነው።››*[6]

---

[5] ሙሉ ሐሳቡን ለመረዳት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያዘጋጀሁትን ‹‹አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ›› የሚለውን መጽሐፍ መመልከት ይጠቅማል።

[6] ገጽ 256።

ለ. ሁለተኛውና በ1996 እ.ኤ.አ *‹‹ኢትዮጵያ፣ ዐረባዊነትና እስልምና በታሪክ ውስጥ››* በሚል ርእስ *በመሐመድ አል ታዩብ ቢን ዬሱፍ አል ዩሱፍ* የተጻፈ ባለ 700 ገጽ መጽሐፍ ሲሆን ካነሣቸው ነጥቦች የተወሰኑትን ለመመልከት እንሞክር፤

*1ኛ) ‹ኢትዮጵያ እስላማዊት ሀገር ናት›* (ዳር አል ኢስላም ናት) የሚለው አመለካከት፦

አክራሪው የወሃቢያ ጸሐፊ ኢትዮጵያ እስላማዊት ሀገር ናት የሚሉት ከአገሪቱ ሕዝብ ‹80 በመቶ› ሙስሊም ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ከዚህ ቀድመው ከተጻፉ የዐረቦቹ ጽሑፎች የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ቁጥር ጣራ ያስነካው፣ 70 በመቶ ናቸው የሚለው፣ በ1935 እ.ኤ.አ ፀረ ኢትዮጵያ አመለካከት አራማጅ ናቸው በሚባሉት በግብጻዊው በዩሱፍ አሕመድ የተጻፈው *‹አል ኢስላም ፊ አል ሐበሻ›* የተሰኘው ሲኾን ከእርሱ ቀጥሎ ደግሞ በብዕር ስም የጻፈው *‹የቆሰለው የኢትዮጵያ እስልምና››* *ደራሲ አቡ አሕመድ አል ኢትዩቢ* ቁጥራቸውን 75 በመቶ ያደርሰዋል፡፡ ይኸኛው ደግሞ ከእነርሱ ቀጥሎ የመጣ፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ቁጥር 80 በመቶ የሚያደርስ ዐይን አውጣ አክራሪ ወሃቢ መኾኑ ነው፡፡[7]

2ኛ) *‹ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ዐረቦች ናቸው›* የሚለው መላ ምት
ጸሐፊው በሁለት ቅጽ (volume) ካዘጋጁት መጽሐፍ ቀላል የማይባለውን ክፍል የኢትዮጵያውያንን *‹የጠራ ዐረብነት›* ለማረጋገጥ አውሎታል፡፡ ይህን የማይቀበሉ ሰዎችንም ‹‹የምሥራቅ አፍሪካ እና የዓባይ ሸለቆን ሕዝብ እና የዐረብን ሕዝብ ታሪክ ነጣጥለው ለማስቀረት የሚሞክሩ ኢምፔሪያሊስቶች ናቸው›› ብሏቸዋል፡፡

---

[7] በዚህ ረገድ በ1987 ዓ.ም የተደረገው ቆጠራ ክርስቲያኖች 61.70 % ክርስቲያን፣ 32.10 ደግሞ ሙስሊም መሆኑን ይመሰክራል፡፡ በርግጥ ሙስሊሞቹ ይህንን ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉበት የግንቦት 1999 ዓ.ም ውጤት ገና ይፋ ባይሆንም በውድም በግድም የቅጥር ማስተካከያ ለማድረግ የሞከሩበት ስለሆነ ውጤቱ በጉጉት እየተጠበቀ ነው፡፡ በ WEDNESDAY, 08 OCTOBER 2008 የታተመው የሪፖርተር ጋዜጣ (http://www.ethiopianreporter.com/content/view/2928/54/) *‹‹የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ በመላው አገሪቱ ያካሄደውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ አጠናቆ ውጤቱን ትናንት መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አስረከበ»* ሲል ዘግቧል፡፡

3ኛ) *‹የአማራ ክርስትና በዓለም ደረጃ እስልምና ላይ የተጠነሰሰው ሤራ አካል ነው›* የሚለው ዘረኛ አስተያየት፣

ጸሐፊው የእስልምና ሃይማኖትን ታጋሽነት ከጠቀሰ በኋላ ምንም እንኳን ታጋሽ ቢኾንም የክርስትናና የአይሁድ ሃይማኖቶች ግን እስልምና ላይ ደባ ከመጠንሰስ ወደ ኋላ እንደማይሉ ያትታል፡፡ *‹‹የክርስቲያኖችና የአይሁድ ብቸኛ ዓላማቸው እስልምናን ማጥፋት፣ ባህሉንና መስጊዶችን ማፈራረስ፣ ምእመኖቹንም /ሙስሊሞቹንም/ ወደ ክሕደት ጎዳና መምራት ነው፡፡ . . . ምንም እንኳን፣ በቁርዐን ላይ እንደ ተጠቀሰው፣ አይሁድና ክርስቲያኖች በመካከላቸው የከረረ ጥላቻ ቢኖርም እስልምናን በተመለከተ ግን ጠላትነታቸውን ዘንግተው በኅብረት እስልምናን ለመዋጋት፣ ለማጥፋትና ምእመናኑን ለመበታተን ይነሣሉ››* ሲል ይዘረዝራል፡፡ የዚህ የክርስትናና የአይሁዳዊነት ስምምነት ትክክለኛ ማሳያ ደግሞ ኢትዮጵያ መኾኗ ነው፡፡ በምሳሌነት የሚጠቀሰውም የነገሥታቷ ከሰሎሞናዊ ትውልድ ጋር መገናኘት፣ እንዲሁም የአሜሪካ መንግሥት በአካባቢው ያለው ፖሊሲ ነው፡፡[8]

4ኛ) *‹‹አሕመድ ግራኝ ያወጀው ጅሃድ የእስልምና ሃይማኖት ጠላቶችን መቋቋሚያ /መግጠሚያ ትክክለኛ መንገድ ነው››* ስለሚለው አስተያየት፣

አክራሪዎች በጠቅላላውም የግራኝ ዘመንን የጅሃድ ዘመቻ፣ የእስልምና ወርቃማ ዘመን አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ዛሬም ቢኾን የኢትዮጵያ እስልምና ራሱን ለመከላከል የሚያደርገውን ‹ቅዱስ ጦርነት› መላው የዓለም ሙስሊም መርዳት አለበት ባይ ነው፡፡

> *የእስልምና ጠላቶች ከጊዜ ጋር እየተሸቀዳደሙ በኢትዮጵያ ያለውን የእስልምና ሃይማኖት ለማውደም ተከታዮቹንም ክርስቲያን ለማድረግ በሚጥሩበት (በአሁኑ ወቅት) የዐረብ መንግሥታት እና ድርጅቶች (ሙስሊሙን) ለመርዳት መነሣት አለባቸው፡፡ ይህ ርዳታ ሲደርሳቸው ሙስሊሞቹ በእምነት (ጠንክረው) ተነሥተው የመስቀል ጦረኞቹን ይቃወማሉ፡፡ . . . ከዚህ ውጭ ይህን ድርጊት ለማከናወን ቸል ማለት ግን እስልምናን አደጋ ላይ ይጥለዋል. . . ስለዚህ ሙስሊሞች ነቅተው እንዲነሡና የሚመጣውን አደጋ ተቋቁመው እስልምናን ከወንጌል ሰባኪዎች እንዲታደጉት ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡*

---

[8] ይህንን ሐሳብ ከሚያራምዱት የጊዜያችን ጸሐፍያን መካከል Dr. Muhammad Shamsaddin Megalommatis የተባሉት የ ‹‹www.americanchronicle.com›› አዘጋጅ አንዱ ናቸው፡፡ ግለሰቡ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ‹‹የአማራ/ የሐበሻ ቤተ ክርስቲያን›› እያሉ ደጋግመው ይጽፋሉ፡፡

5ኛ) *‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ተሐድሶ ሊደረግበት ይገባል። ይህ ሲደረግ ግን መኾን ያለበት በምሥጢር ነው››* ስለሚለው *(ሙስሊሞችን ድጋሚ የማስለም)* የምሥጢር አጀንዳ፣

አክራሪዎች በሙሉ እንደሚጽፉትና እንደሚያስተምሩት *‹‹በኢትዮጵያ ለዘመናት የቆየው የሱፊ እስልምና ትክክለኛ ባለመኾኑ መወገድ አለበት››*። ይህንንም ለማድረግ፣ ለምሳሌ በሐረር የሚኘውን የአውቢዳል ተቋም በመጥቀስ፣ የሚከተሉትን መፍትሔዎች ይጠቁማል።

- *የአገሬውን የእምነቱ አስተማሪዎች በድጋሚ ማሠልጠንና ማስተማር፣ ምክንያቱም ታዋቂ የተባሉት ሊቃውንትም እንኳን ቢኾኑ በዘመናዊ መንገድ የተማሩ ባለመኾናቸው፣*
- *የዕውቀት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ተማሪዎችን በተገቢውና በዘመናዊ መንገድ በማሠልጠን የሚመጣባቸውን ፈተና እንዲቋቋሙ ማድረግ፣*
- *በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ መድራሳዎችን ጠላት ሊያይና ሊነቃ በማይችልበት መንገድ በምሥጢር መርዳት። ይህንንም ለማድረግ ማኅበረሰቡን ከሚያስተዳድሩ የየአካባቢው የእምነቱ መሪዎች ጋር መተባበር፤*

በአጠቃላይ ኢትዮጵያን በተመለከተ በተለይ በ1990ዎቹ እ.ኤ.አ የወጡ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የኅትመት ውጤቶች ቢኖሩም ዋና ሐሳባቸው ግን ከፍ ብለን ከዘረዘርነው ጋር ተመሳሳይ ነው።

## *4ኛ) አክራሪ እስልምና የደቀነውን አደጋ ለመቋቋም ምን ማድረግ አለብን?*

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሰፊ ሥራ እንደሚጠይቅ ሳይታለም የተፈታ ነው። ከታሰበ ቀርቶ ከተወረወረ በሚያድነው በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በእናቱ አማላጅነት፣ በቅዱሳኑ ረዳትነት እንደምናልፈው ብናምንም ከእኛ የሚጠበቀውን ለመፈጸም ግን መዘጋጀትና መሥራት ይገባልና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ናቸው የምላቸውን ዐበይት ነጥቦች ለማቅረብ እሞክራለሁ።

በእኔ አመለካከት አክራሪነቱን በመከላከሉ ረገድ ድርሻ ሊኖራቸው የሚችሉ ሦስት አካሎች አሉ፡፡ እነርሱም ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና በጎ ኅሊና፣ ቀና ስብዕና ያላቸው ሙስሊሞች ናቸው፡፡ የሦስቱ መተባበር፣ ለአንድ ግብ መሥራት ሁነኛ ለውጥ ያመጣል፡፡ ከሁሉም ግን ዋነኛው ኃላፊነት የሚወድቀው በቤተ ክርስቲያን ላይ በመሆኑ የርሷና የተቀሩት የሁለቱ ኃላፊነት በጭራሽ የሚወዳደር አይደለም፡፡

ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ መሠራት ያለበትን ሥራ ስንዘረዝር የመፍትሔው አካል የሚሆኑ ሦስት አካላትን እናገኛለን፡፡ እነርሱም ጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ ማኅበረ ካህናቱና ምዕመናን ናቸው፡፡ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የቤተ ክርስቲኒቱን ሃይማኖታዊና አስተዳደራዊ መሪነት የጨበጠ አካል እንደመሆኑ የአክራሪነቱን አደጋ አውቆ መንቃትና መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ከጅማው ጭፍጨፋ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የአደጋውን አሳሳቢነት በመረዳት ይህንኑ ጉዳይ የሚከታተል ኮሚቴ ማዋቀሩ እሰይ የሚያሰኝ ነው፡፡ ግርግሩ የአንድ ሰሞን ብቻ እንዳይሆን ግን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመሥራት መጣር ይጠበቅበታል፡፡

ሁለተኛው የመፍትሔ አካል ማኅበረ ካህናቱ ነው፡፡ የችግሩ የመጀመሪያ ተጠቂ የሚሆነውም እርሱ ነው፡፡ በግራኝ ዘመን፣ በጣሊያን ወረራም ሆነ በጅማው የአቡነ ገ/መ/ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ጥቃት በመጀመሪያ የታረዱት ካህናቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ችግሩን ለመቅረፍ ፈጥነው ተነሥተው ምዕመኑን መምራትና አቅጣጫ ማስያዝ ያለባቸውም እነርሱው ናቸው፡፡ ካህናቱ ከመተባበር ውጪ እንደከዚህ ቀደሙ በውኃ ቀጠነ ለመለያየት ምንም ዕድል ያላቸው አይመስልም፡፡ የምንናናቅበት፣ የምንከፋፈልበት ጊዜ አይደለም፡፡ የመጣው ጠላት እንደ መናፍቃኑ በስብከት ብቻ የሚመለስ አለመሆኑን በአርሲ፣ በጅማ፣ በሐረርጌ፣ በምዕራብ ወለጋና በወሎ ከሚሴ በቅጡ አሳይቶናል፡፡ አክራሪነት ከደቀነው አደጋ አንጻር በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ተቀራርበው እንዳይሠሩ ሊያደርግ የሚችል ዐቢይ አጀንዳ ብዬ አልገምትም፡፡ በተለይም በዳያስጶራ የሚገኙ አገልጋዮች የሃይማኖት ወንድሞቻቸው፣ የክህነት እኩዮቻቸው የሆኑት አበው ካህናት፣ ወንድሞች ዲያቆናት እንዲሁም የአብነት ተማሪዎች የተጋረጠባቸውን ፈተና ተገንዝበው ለእነርሱ ሲሉ በኅብረት ሊሠሩ ይገባቸዋል፡፡

ምዕመኑ እስካሁን ያሳየውን ትጋትና ንቃት ከቀጠለ በተለይም በዕውቀት ራሱን እንዲያጎለብት ርዳታ ካገኘ ድህነቱንም ተቋቁሞ በእምነቱ ለመዝለቅ ይችላል፡፡ ለዚህ ግን የቤተ ክህነቱና በጠቅላላው የማኅበረ ካህናቱ መሪነት ያስፈልገዋል፡፡ ምዕመኑን በማስተባበርና በመምራት በኩል ወጣት የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ አክራሪዎች በዋነኝነት የሚጠቀሙበት፣ አዕምሮውን አበላሽተው ለክፉ ዓላማቸው የሚልኩት ሙስሊሙን ወጣት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ወጣት ልጆቿን በሃይማኖት አሰልጥና ካበረታች ለሃይማኖታቸው ዘብ ለመቆም ወደ ኋላ አይሉም፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከሌላ አካል መፍትሔ ከመፈለጓ በፊት ውስጧን ያዳከመውን መለያየትና የአስተዳደር ብልሹነት ማስተካከል ይጠበቅባታል፡፡ ከመንግሥትም ጋር ሆነ አክራሪነትን ከማይቀበለው ሙስሊም ኅበረተሰብ ጋር ለመወያየት በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ማስከበር መቻል አለባት፡፡ ቀጥሎ ሀገሪቱን ከሚያስተዳድረው መንግሥት ጋር ስለ ችግሩ መነጋገር አለባት፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ የመንግሥቱን ሥልጣን የያዙ ብዙ ባለሥልጣኖች ወንበራቸውን መከታ አድርገው ቤተ ክርስቲያኒቱን እየገፉ ነው፡፡ ይህንን የመሰለውን ቅጥ ያጣ አሠራር ከሚመለከተው ባለሥልጣን ጋር ለመነጋገር አፋራምነቷን ትታ መነሣት አለባት፡፡ ገና ለገና ፖለቲካ ውስጥ ገባሽ እባላለሁ በሚል የዋህነት ልጆቿ በመቅደሳቸው ሲታረዱ እያየች እንዳላየች መሆን አይጠበቅባትም፡፡

በሦስተኛ ደረጃ አክራሪነትን ሊያመክኑ ከሚችሉት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችም ጋር ተባብሮ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ አክራሪዎቹ እነርሱንም ቢሆን ድጋሚ ለማስለም እንደሚፈልጉ በማስረዳት፣ በሌሎች አገሮች የሆነውን በአብነት በማስረዳት ከእኛ ጋር ቢተባበሩ ለእምነታቸውም ቢሆን እንደሚበጅ ማስረዳት ይጠበቅብናል፡፡ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኙ ካህናትና ምዕመናን በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የሚያደርጉት መሰባሰብ በአክራሪዎች እንዳይጠለፍ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አክራሪ ኃይል አይዞህ የሚሉት በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በካናዳ እንዲሁም በተለያዩ የዐረብ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ የሳዑዲ ወሐቢያዎች እያሰለጠኑ መሣሪያቸው እያደረጉ ያሉት የእኛኑ ወገን ነው፡፡ ክርስቲያኖቹ ተከፋፍለን ‹‹ስደተኛ፣ ገለልተኛ፣ ቀጥተኛ›› ስንባባል እነርሱ ግን በአንድነት ተሰልፈው

በወጣቶች፣ በሴቶች፣ በወንዶች ተደራጅተው የሚሰበሰቡት ስለ ቤተ ክርስቲያን ጨቋኝነት ለመነጋገር ነው። ይህንን ለመረዳት የሚከተሉትን የመገናኛ ብዙኃንና ማኅበራት መመልከቱ በቂ ነው።

1ኛ)በድር ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ፌዴሬሽን - Badr International Ethiopian Muslims Federation (http://www.ethiopianmuslimsfederation.com)

2ኛ)የአውሮፓ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ኔትወርክ (www.ethiopianmuslims.net)[9]

3ኛ)ነጋሺ ድረ ገጽ (http://blog.ethiopianmuslims.net/negashi/)

4ኛ)ሬዲዮ ነጋሺ ስዊዲን (http://radionegashi.ethiopianmuslims.net/)

5ኛ)ፈርስት ሒጅራ ፋውንዴሽን (First Hijra Foundation (Washington DC))

6ኛ)የፈርስት ሒጅራ ሬዲዮ (http://wmet1160.com/schedule/first_hijrah/)

7ኛ)የኢትዮጵያውያን ካናዳውያን ሙስሊም ማኅበረሰብ ማኅበር (The Ethiopian Canadian Muslim Community Association) http://www.ethiopianmuslims.com/index.htm

በአጠቃላይ አክራሪ እስልምና የጋረጠብን አደጋ ያህል በአንድነት ጠንክረን መሥራት ከቻልን ግን ጭከና የተሞላበት የአክራሪነት እንቅስቃሴ ኀሊናቸውን የሚቆረቁራቸውን ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ወንጌል ለማቅረብ ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል። ኢሰብዓዊ ጭካኔ የጸናባቸው በብዙዎች የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች የሚገኙ ሙስሊሞች እንደ ኒቆዲሞስ በየሌሊቱ ክርስቶስን ፍለጋ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሚመጡ ስንረዳ በአገራችንም የተሻለ ዕድል መኖሩን እንድንገነዘብ ያደርገናል። ስለዚህ ገዳሞቻችን እያጠናከርን፣ የአብነት ተማሪዎቻችንን እየደጎምን፣ ካህናቱን እያበረታን፣ ወጣቶችን በሰ/ት/ቤቶች አእንዲታቀፉና እንዲያገለግሉ እየመራን ከሄድን የዛሬውነ ችግር አልፈን ለልጆቻችን እምነታችንን ልናወርስ እንችላለን። ይህንን ካላደረግን ግን አክራሪዎቹ በስልጤ ዞንና በብዙ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች እያደረጉ እንዳሉት ሀገራችንን እየተቆጣጠሩ እንደሚሄዱ መገመት የሚከብድ አይሆንም ። እግዚአብሔር ከዚህ ይሰውረን። አሜን።

[9] The "Network of Ethiopian Muslims in Europe" (NEME) is an initiative of brothers from different parts of Europe with the objective of bring together Ethiopian Muslim Communities and individuals of the various European Countries. It is also the mission of NEME to help set up such a community in countries where there is none yet.